የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፳፫
አዲስ አበባ ሰኔ ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

29th Year No. 23
ADDIS ABABA, 20th June, 2023


## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፺፩/፪ሺ፲፭


በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች መንግሥት መካከል የተደረገውን የአሳልፎ መስጠት ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ................................ገጽ ፲፬ሺ፯፻፷


## Content

Proclamation No. 1291/2023


Extradition Treaty between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the United Arab Emirates Ratification Proclamation ……......................................................Page 14760


### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፺፩/፪ሺ፲፭

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች መንግሥት መካከል የተደረገውን የአሳልፎ መስጠት ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች መንግሥት መካከል መስከረም ፲፩ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም በአቡዳቢ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህን ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፰ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም በአካሄደው ፲፱ኛ መደበኛ ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፣

### PROCLAMATION NO. 1291/2023

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE EXTRADITION TREATY BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE UNITED ARAB EMIRATES**

**WHEREAS,** the Extradition Treaty between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the United Arab Emirates has been signed in Abu Dhabi, on the 21st September, 2022;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said agreement at its 19th ordinary session held on 16th Day of May, 2023;


ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች መንግሥት መካከል የተደረገውን የአሳልፎ መስጠት ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፺፩/፪ሺ፲፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ስምምነቱ ስለመጽደቁ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች መንግሥት መካከል መስከረም ፲፩ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም በአቡዳቢ የተፈረመው የአሳልፎ መስጠት ስምምነት ፀድቋል፡፡

**፫. የኢፌዲሪ የፍትሕ ሚኒስቴር ኃላፊነት**

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፍትሕ ሚኒስቴር ይህን ስምምነት ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ሁሉ እንዲወስድ በዚህ አዋጅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

**አዲስ አበባ ሰኔ ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Sub-Articles (1) and (12) of Article 55 the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Extradition Treaty between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the United Arab Emirates Ratification Proclamation No.1291/2023".

**2. Ratification of the Agreement**

The Extradition Treaty signed in Abu Dhabi on the 21st of September 2022 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the United Arab Emirates, is hereby ratified.

**3. Responsibility of the FDRE Ministry of Justice**

The FDRE Ministry of Justice is hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Treaty.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall come into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, On this 20th Day of June, 2023**

**SAHLE-WORK ZEWDIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**